በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሠ/መ/ቁጥር 201974

ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ ታደሰ ንጉሴ

ተጠሪ ፡- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ሻሸመኔ ቅርንጫፍ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ከተጠሪ ጋር በ1989 ዓ/ም በፈፀሙት የስራ ውል በባላንስ ሠራተኛነት የስራ መደብ ላይ በወር 13,034.00 እየተከፈላቸዉ እንዲሰሩ ተቀጥረዉ ሲሰሩ መቆየታቸዉን፤ነገር ግን ያለምንም ምክንያት በቀን 07/09/2011ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የትራንዛክሽን ሥራ በመስራት በማሳለፍ ብድር በመዝጋት ባንኩ ማግኘት ያለበትን በማሳጣት ጥፋት ፈጽመሀል በማለት ሥራዬ ትራንዛክሽን ማሳለፍ ባለመሆኑ የሰራሁት ጥፋት ሳይኖር ከሕግ-ዉጭ ከሥራ አሰናብቶኛል፡፡ስለሆነም ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ እንዲወስንልኝ፡፡ይህ የሚታለፍ ከሆነ የስንብት ክፍያ ብር 95,582.67 ፤የ15 ቀን ደመወዝ ብር 6,517.00 ፤ክፍያ ለዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ ብር 39,102.00 ፤ካሳ የ6 ወር ደመወዝ ብር 78,204.00፤የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ብር 63,550.29፤ተጠሪ ባንክ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ከ20 ዓመት በላይ ላገለገለ ሰራተኛ 21 ካራት ወርቅ ስለሚሰጥ የዚህ ዋጋ የአንድ ካራት ዋጋ ብር 1,700.00 ብር 35,700.00፤የቦነስ ክፍያ የ2011 ዓ/ም ብር 39,102.00፤ከ2009-2011ዓ/ም ድረስ ያልተጠቀምኩበትን የሶስት ዓመት የአመት እረፍት ወደገንዘብ ቀይሮ እንዲከፍለኝ በአቃላይ ብር 370,991.29 (ሶስት መቶ ሰባ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አንድ ብር ከሃያ ዘጠኝ ሳንቲም) እንዲከፈላቸዉ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠዉ መልስ አመልካች በተጠሪ መስሪያ ቤት በካሼርነት የስራ መደብ ተቀጥረዉ በሚሰሩበት ወቅት የባንኩ ደንበኛ የሆኑት መሀመድ ተካ ብድር ወስደው የነበረውን ገንዘብ መመለስ ስላልቻሉ በዋስትና የተያዘውን ንብረት ለመሸጥ የወጣው የጨረታ ማስታወቂያ አንድ ቀን ሲቀር በቀን 18/07/2018 እ.እ.አ ከቅርንጫፉ ስራ አስኪያጅ ጋር በመሆን ባለእዳው በቼክ 700,000.00(ሰባት መቶ ሺህ ብር) ገቢ እንዳደረጉ አስመስለዉ የሀሰት ሂሳብ አሳልፈዉ ለጨረታው እንቅፋት ፈጥረዋል፡፡ በአመልካች ድርጊት ተጠሪ ብር 4,794.52 አጥቷል፡፡ አመልካች በቀን 11/11/2010 ዓ/ም በሀሰት ገቢ የሆነውን ብር ቆጥሬ ተቀብያለሁ በማለት ኦፊሰር ይህንን ገንዘብ ገቢ እንዲያደርግ አድርገዋል፡፡ነገር ግን ገንዘቡ ገቢ የሆነበት ቀን ሲታይ ብር 350,000.00 በቀን 23/11/2011ዓ/ም ገቢ የሆነ ሲሆን ሌላዉ ብር 350,000.00 ገቢ የሆነዉ በቀን 350,000.00 ነዉ፡፡አመልካች ገንዘቡ ገቢ የሆነባቸዉን ኦርጅናል ሰነዶች እንዲጠፉ አድርገዋል፡፡አመልካች የፈጸሟቸዉ ድርጊቶች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27(1/ሐ) እና በባንኩ የሠራተኞች የሥራ ሂደት ፖሊሲ ቁጥር 1/ለ አንቀጽ 1/1 መሰረት በከባድ ማታለል ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያስናበት ጥፋት በመሆኑ አመልካችን በማሰናበት የተወሰደዉ እርምጃ ሕጋዊ ነዉ፡፡ስለሆነም አመልካች ወደሥራ ሊመለስ አይገባም እንዲሁም ሕገ-ወጥ ስንብት ተፈጽሟል በሚል የጠየቋቸዉ ክፍያዎችም ሊከፈላቸዉ አይገባም፡፡በባንኩ አሰራር መሰረት ደመወዝ የሚከፈለዉ በአዉሮፓ አቆጣጠር ወር በገባ በ20ኛ ቀን ላይ ጀምሮ በመሆኑ እስከ ቀን 20/06/2011ዓ/ም ድረስ ያለዉ የግንቦት ወር ደመወዝ ስለተከፈላቸዉ ያልተከፈለ ደመወዝ የለም፡፡ያልተከፈለ ደመወዝ መኖሩን በመግለጽ ለተጠሪ ያመለከቱት ነገር ባለመኖሩ ክፍያ ዘግይቷል በሚል የጠየቁት ሊከፈላቸዉ የሚገባ አይደለም፡፡ዉሉ የተቋረጠዉ የቦነስ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በቀን 07/09/2011ዓ/ም ስለሆነ ቦነስ ሊከፈላቸዉ አይገባም፡፡ አመልካች ብድር ስላለባቸዉና በብድር ዉሉ መሰረት ሠራተኛዉ ስራ ሲለቁ ከማንኛዉም ተከፋይ ክፍያ(ከፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ) ላይ ጭምር ተቀንሶ እንደሚከፈል ስለተመለከተ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያቸዉ ለእዳቸዉ ገቢ ሆኗል፡፡አመልካች የ60.5 ቀን የአመት እረፍት እንዳላቸዉ ባይካድም ሊከፈላቸዉ የሚገባዉ የባንኩን አሰራር በመከተል ያለባቸዉን እዳ ብር 294,429.66 ከፍለዉ ክሊራንስ ሲያቀርቡ ነዉ፡፡ያቀረቡት የወርቅ ሽልማት ጥያቄ የሕግ መሰረት የለዉም በማለት መልሳቸዉን በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 09416 ላይ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማትና ማስረጃዎችን በመመርመር በቀን 06/05/2012 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገዉ የሥራ ዉል ለማቋረጥ ምክንያት የሆነዉ የባንኩ ባለዕዳ እዳዉን መክፈል ባለመቻሉ ባንኩ በመያዣነት የተያዘዉን ንብረት ለመሸጥ ጨረታ አዉጥቶ እያለ አመልካች ባለዕዳዉ ብር 700,000.00 ገቢ እንዳደረገ በማስመሰል ትራንዛክሽን በማስተላለፍ ባንኩ የወጣዉ ጨረታ ሂደት እንዲቋረጥ በማድረግ ጥፋት መፈጸሙ በኦዲት ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የትራንዛክሽን መደብ ሠራተኛ ሳይሆኑ ገንዘብ ያዥ እንደሆኑ ተጠሪም አልካደም፡፡ ስለዚህ አመልካች ይህን ሂሳብ መዝጋታቸዉን የሚያሳይ ማስረጃ የለም፡፡ አመልካች ሲሰሩ በነበሩበት የሥራ መደብ ላይ የፈፀሙት ጥፋት የለም፡፡ የገንዘብ ማስተላለፍም ሆነ ጨረታን መዝጋት ሥራ የአመልካች ድርሻ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ለሥራ ውል መቋረጥ ምክንያት የሆነው ገንዘብ ለተጠሪ መስሪያ

ቤት ገቢ መሆኑንም ተጠሪ አምኗል፡፡ በመሆኑም የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕገ-ወጥ መንገድ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43 መሰረት ተጠሪ አመልካችን ወደ መደበኛ ሥራቸዉ እንዲመልሳቸዉና ከሐምሌ እስከ ጥር 2012 ዓ/ም ድረስ ያለዉን ደመወዛቸዉን እንዲከፍላቸው ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 41159 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 26/08/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ውሳኔ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

በመቀጠል ተጠሪ የሰበር አቤቱታውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው ችሎቱም በመ/ቁጥር 336132 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 15/03/2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ በስር የቀረበው የኦዲት ውጤት ማስረጃ ተጠሪ የስራ ድርሻዬ የእዳ ገንዘብ ማስከፈል አይደለም ይበሉ እንጂ ደረቅ ቼክ በመውሰድ ባለእዳው እዳውን እንደከፈለ በማስመሰል ጨረታው እንዲሰረዝ ማድረጋቸዉንና ደንበኛው ያለበትን እዳ ካዘጋ በኋላ ደንበኛው ያለበትን ብድር 2ኛ ዙር ክፍያ እዳ መክፈሉን የኦዲት ሪፖርቱ ያረጋግጣል፡፡ዋናው እዳ ቢከፈልም ተጠሪ ሊያገኝ የሚገባውን በማጣቱ የኢኮኖሚ ጉዳት ደርሶበታል፡፡የሥር ፍርድ ቤት ጨረታዉ እንዲሻር ያደረገዉ የባንኩ ሥራ አስኪያጅ መሆኑን እንጂ አመልካች ጥፋት መፈጸሙን የኦዲት ሪፖርቱ አያሳይም ያለ ቢሆንም ከተጠሪዉ ቅርንጫፍ ሥራ አሲኪያጅ ጋር በመሆን ደረቅ ቼክ በመቀበል እዳ ካዘጋ በኋላ ደንበኛዉ ያለበትን ብድር የ2ኛ ዙር ክፍያ መክፈሉ ቢረጋገጥም አመልካች በተጠሪ ላይ የብር 4,794.52 የኢኮኖሚ ጉዳት እንዲደርስበት አድርገዋል፡፡ስለሆነም አመልካች በተጠሪ ላይ የኢኮኖም ጉዳት በማድረሳቸዉ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 27(1/ሸ) መሰረት ያለማስጠንቀቂያ የሚያሰናብታቸዉን ጥፋት ፈጽመዋል፡፡በተጨማሪም አመልካች ደረቅ ቼክ በመቀበል በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1/ሐ) መሰረት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብታቸዉን የማታለል ድርጊት ፈመዋል፡፡ስለሆነም ተጠሪ አመልካችን ያሰናበተዉ በሕግ አግባብ ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ አመልካች በቀን 27/05/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ መልኩ በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

አመልካች የተቀጠርኩበት የሥራ መደብ የካሼር የሥራ መደብ ሲሆን የሥራ ድርሻዬ ደግሞ ገንዘብ በካዝና ቆጥሮ ማስቀመጥ፣ካሽ ከሲስተም ጋር በማገናዘብ ወጪና ገቢ ሚዛናዊ(ባላንስ) መሆኑን ማረጋገጥ መሆኑን የሥራ ዉሌ የሚያሳይ ሲሆን ተጠሪም ከሥር ጀምሮ ይህንን አልካደም፡፡አመልካች ገንዘብ ትራንዛክት የማድረግም ሆነ ብድር የመዝጋት ሥልጣን የለኝም፡፡በጨረታዉ ላይም አልተሳተፍኩም፡፡ተጠሪ ያሰናበተኝ ትራንዛክሽን በማሳለፍ እና ብድር በመዝጋት ባንኩ ማግኘት የሚገባዉን ብር 4794.52 አሳጥቷል በማለት ቢሆንም ያሰናበተኝ የሥራ ድርሻዬን ወደ ጎን በመተዉ በመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 92466 ላይ የተሰጠዉት የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ስንብቱ ከሕግ ዉጭ ነዉ፡፡ገንዘብ ትራንዛክሽን የሚደረገዉ የሚስጥር ቁጥር ባለዉ የትራንዛክሽን ሠራተኛ ሲሆን ብድር የሚዘጉትም ይህ የሥራ መደብ የሚመለከታቸዉን

ኃላፊዎች እንደሆነ የተረጋገጠ ሲሆን በማንኛዉም የባንኪንግ አገልግሎት የሚሰራበት አሰራር ነዉ፡፡ቼኩንና የተለያዩ ሰነዶችን ደብቋል የተባልኩትም በማስረጃ ካለመረጋገጡም በላይ የሥራ ድርሻዬን የሚመለከት አይደለም፡፡የሻሸመነ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ከተበዳሪዉ የተከፈለዉን ብር 700,000.00 በራሳቸዉ ፊርማ ገቢ አድርገዋል፡፡ተጠሪ ከሥራ ያሰናበተኝ ድርጊቱ ተፈጸመ ከተባለ ከአንድ አመት በኋላ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/3 ስር በተደነገገዉ መሰረት በ30 ቀን በኋላ የተወሰደ እርምጃ በመሆኑ በይርጋ የታገደ ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ስንብቱ በሕግ አግባብ የተፈጸመ ነዉ በማለት የስራ መደቤንና የሥራ ድርሻዬን ወደ ጎን በመተዉ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ጥፋት አጥፍቷል የተባለበት የስራ መደብና እሳቸው የሚሰሩት የስራ መደብ ቦታ ተዛማጅነት ያለው መሆን አለመሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ የሥራ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ ተብሎ የተወሰነበትን አግባብነት ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 15/08/2013ዓ/ም የተጻፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

አንድ የባንኩ ተበዳሪ እዳዉን ባለመክፈሉ ምክንያት ባንኩ በመያዣነት የያዘዉን ንብረት በጨረታ ለመሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ አዉጥቶ ጨረታ ሊደረግ አንድ ቀን ቀርቶ እያለ አመልካች ከተበዳሪዉ ለምን ደረቅ ቼክ ተቀብለን ብድሩን አንከፍልለትም በማለት በወቅቱ የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ለነበሩት የማጭበርበር ሀሳብ በማቅረብና በመስማማት በተበዳሪዉ ሂሳብ ዉስጥ ገንዘብ ሳይኖር ደረቅ ቼክ በመቀበል ለዚህ ሀሰተኛ ትራንዛክሽን እንዲመች ወደሂሳቡ ጥሬ ገንዘብ ገቢ ማድረጊያ ቅጽ በመሙላት ብር 700,000.00 ከተበዳሪዉ ሂሳብ ገቢ እንደሆነ በማስመሰል የደንበኞች ኦፊሰር አስፈርመዉ ትራንዛክሽኑ ፖስት እንዲደረግ ማድረጋቸዉ ተረጋግጧል፡፡አመልካች አሁን ላይ የሲስተም መጠቀሚያ ፓስወርድ የለኝም የሚሉት ካጠፉት ጥፋት ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡ስንቅ የሌለዉ ቼክ እንዲጻፍ ሀሳብ ከማቅረብ ጀምሮ ስለተሳተፉ የሲስተም ፓስወርድ እንዲጠቀሙ የሚያስገድዳቸዉ ሁኔታ ባለመኖሩና በእለቱ የእለት ቲኬቶች ጠቅለለዉ ሲይዙ የነበሩትም አመልካች ስለነበሩ ጉዳዩ ከእሳቸዉ ሥራ ጋር እንደማይገናኝ በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡የአመልካች ስራ ካሽ በካዝና ቆጥሮ ማስቀመጥና ከኮምፒዉተር ሲስተም ጋር ማገናዘብ እና ሚዛናዊ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሆነ ቢገልጹም በካዝና ዉስጥ ያለ ገንዘብ አረጋግጦ ማስቀመት ቀርቶ ገቢ ያልሆነን ገንዘብ ደረቅ ቼክ በመቀበል ገቢ እንደሆነ በማስመሰል የማይጠበቅባቸዉን ተግባር ፈጽመዋል፡፡የእለቱ ሂሳብም ባላንስ አለመሆኑን ለስር ፍርድ ቤት አስረድተናል፡፡ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ከዚህ አንጻር ተመርምሮ ጥፋቱ የአሁን አመልካች መሆኑ ተረጋግጦ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡አመልካች ይርጋን አስመልክቶ ያነሱት መከራከሪያ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 329/1 መሰረት ተቀባይነት ሊኖረዉ አይገባም፡፡አመልካችም በቀን 26/08/2013ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የየዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች ተቀጥረዉ ሲሰሩ የነበረዉ የሥራ መደብ የካሼር መደብ(የገንዘብ ያዥነት የሥራ መደብ) እንደሆነ ተጠሪ አልካደም፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን የተመለከተዉ ፍርድ ቤት እና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምረዉና መዝነዉ አመልካች ገንዘብ ያዥ(ካሼር) እንጂ የትራንዛክሽን መደብ ሠራተኛ እንዳልሆኑ፤ የገንዘብ ማስተላለፍም ሆነ ጨረታን መዝጋት ሥራ የአመልካች ድርሻ አለመሆኑንና ከዚህ ጋር በተያያዘ ተጠሪ አመልካችን ሲያሰናብት አመልካች የፈጸሙት ጥፋት ነዉ የተባለዉን ድርጊት አመልካች የፈጸሙ ስለመሆኑ ተጠሪ ባቀረቡት ማስረጃ አላስረዱም በሚል ተጠሪ አመልካችን ከሕግ-ዉጭ አሰናብቷል የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ተጠሪ ዉዝፍ ደመወዝ በመክፈል አመልካችን ወደ ሥራ ገበታቸዉ እንዲመልስ ወስነዋል፡፡

ዋናዉን ክርክር ከመመርመራችን በፊት አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/3 ስር የተደነገገዉን ይርጋ አስመልክቶ ያነሱትን ክርክር ተመልክተናል፡፡በዚህ ድንጋጌ ላይ አንድ አሠሪ ዉሉን ለማቋረጥ የሚያስችል በአዋጁ አንቀጽ 27/1 ስር የተመለከተ ምክንያት መከሰቱት ካወቀብ ቀን ጀምሮ ባለዉ 30 ቀን ዉስጥ ዉል የማቋረጥ እርምጃ ካልወሰደ መብቱ በይርጋ እንደሚታገድ ተደንግጓል፡፡ይህ ይርጋ የተጠሪን ዉል የማቋረጥ መብት የሚያሳጣ በመሆኑ አመልካች ምክንያቱ የተከሰተበትን ቀን እና ተጠሪ ምክንያቱ የተከሰተበትን ቀን መቼ እንዳወቀ በማሳየት ለስር ፍርድ ቤት በሥነ ሥርዓት ሕጉ አግባብ በግለጽ ክርክር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ሆኖም በዚህ መልኩ ለስር ፍርድ ቤት ክርክር ማቅረባቸዉን የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ አያሳይም፡፡ይህንን መከራከሪያ ለስር ፍርድ ቤት አቅርቤያለሁ በማለት በመልስ መልሳቸዉ ላይ ያነሱ መከራከሪያም የለም፡፡በመሆኑም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ መሰረታዊ ሕግ ላይ ያለን የይርጋ መቃወሚያ በማንሳት ለመከራከር ስለማይቻል ከዚህ አኳያ ያቀረቡትን አቤቱታ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 329/1 መሰረት አልተቀበልንም፡፡

በሌላ በኩል እንደሚታወቀዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 እና በተሻሻለዉ የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 64(2/ሐ) ስር እንደተመለከተዉ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ሆነ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ሥልጣን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ዉሳኔ እንዲያርሙ ነዉ፡፡ ሰበር ችሎት የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትንና ተቀባይነትን (Production,relevancy and admissibility of evidence)እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን (weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች ተጥሶ በግልጽ ተጥሶ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ መኖሩን አረጋግጦ ስህተቱ እንዲታረም ሊወስኑ ከሚችሉ በስተቀር

ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ ለመቀበል፣ለመስማትና ለመመዘን ሥልጣን ለተሰጣቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች አቅርበዉ ተመርምረዉ የተመዘኑትን ማስረጃዎች በድጋሚ የመመዘን ተግባር ዉስጥ በመግባት ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን አከራካሪ የሆነዉ ፍሬ ነገር መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥልጣን የላቸዉም፡፡በመሆኑም ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃዎችን የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን የተሰጣቸዉ የሥር ፍርድ ቤቶች የቀረቡላቸዉን ማስረጃዎች መርምረዉና መዝነዉ ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር ወደ ጎን በመተዉ ማስረጃ በመመርምርና በመመዘን በፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ በመድረስ የሚሰጠዉ ዉሳኔ በሕግ ከተሰጠዉ ሥልጣን ዉጭ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን የተመለከተዉ የወረዳ ፍርድ ቤት እና ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመርመርና በመመዘን የአመልካች የሥራ መደብ ገንዘብ ያዥነት እንደሆነ፣አመልካች ገንዘብ የማስተላለፍ (የትራንዛክሽን) የሥራ መደብ ሠራተኛ እንዳልሆኑና ገንዘብ የማስተላለፍ ተግባር የሥራ ድርሻቸዉ እንዳልሆነ፣ከብድር ገንዘብ አከፋፈልም ሆነ የተበዳሪዉን ንብረት በጨረታ ለመሸጥ የወጣ ጨረታ እንዲቋረጥ ከማድረግ ጋር በተያያዘ አመልካች የሥራ ድርሻቸዉ ስላልሆነ ሚና እንዳልነበራቸዉና ፈጸሙ የተባለዉን ጥፋት ስለመፈጸማቸዉ ተጠሪ ባቀረባቸዉ ማስረጃዎች አለማስረዳቱን በማረጋገጥ ተጠሪ አመልካችን በሕገ-ወጥ መንገድ አሰናብቷል በማለት የሰጡት ዉሳኔ ከማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር አንጻር ጉድለት አለበት ሊባል የሚችል አይደለም፡፡በሌላ በኩል የክልሉ ሰበር ችሎት በተጠቀሰዉ መሰረት በሕግ ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን የተሰጣቸዉ የሥር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር ወደ ጎን በመተዉ በራሱ ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን አመልካች በተጠሪ የኢኮኖሚ ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረሳቸዉና የማታለል ድርጊት መፈጸማቸዉ ተረጋግጧል የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ተጠሪ አመልካችን ያሰናበተዉ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1/ሐ እና ሸ) መሰረት በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ ከማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር አንጻር በስር ፍርድ ቤቶች የተፈጸመ ስህተት መኖሩን የማያሳይና በሕግ ከተሰጠዉ ሥልጣን ዉጭ ማስረጃ የመመዘን ተግባር ዉስጥ በመግባት የሰጠዉ ዉሳኔ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የሻሸመኔ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 09416 ላይ በቀን 06/05/2012 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እና የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 41159 ላይ በቀን 26/08/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንተዋል፡፡

2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 336132 ላይ በቀን 15/03/2013 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

# <u>ት እ ዛ ዝ</u>

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ